# “በኢትዮጵያ ለቤት ውስጥ ፍጆታና ለማምረቻ አገልግሎት የሚሆን ቀጣይነት ያለው የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ማበረታቻ” ፕሮጀክት

በገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የፈጠራ ስራዎች ሽልማት መወዳደሪያ መመሪያና ማመልከቻ

**ሚያዚያ 13፣ 2009 ዓ.ም**

## ማውጫ


1. መግቢያ ……………………………………………………………………..…..……...1
2. ትርጉም……………………………………………………………………………....1
3. ዓላማ ………………………………………………………………………..……....2
4. የሽልማት ዘርፎች/ምድቦች ………………………………………………………..…..2
5. በውድድሩተሳታፊ ለመሆን የሚያስችሉ መስፈርቶች………………………..………………..…..3
6. የሽልማቱጥቅል……………………………………………………………….......3
7. የማመልከት ሂደት …………………… ……………………………………………..…..4
8. የማመልከቻ ጊዜ ………………………………………………………………..…..4
9. ማመልከቻ ማስገቢያ ቦታ ………………………………………………………......4
10. የአመራረጥ ሂደት …………………………………………………………………...5
    10.1. የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ………………………………………………………..5
    10.2. ዋና/የመጨረሻ ማጣሪያ ………………………………………………….…………5
11. የሽልማት ዳኞች …………………………………………………………………....5
12. ውሳኔን ማስፀደቅ ……………………………………………………………...…....6
13. የመምረጫ መስፈርት ..…………………… ………………………………………...6

መግለጫ ሀ፡ የማመልከቻ ቅፅ (ለገጠር ኢነርጂ/ሃይል የፈጠራ ስራዎች ብቻ) ……........…………..............9

መግለጫ ለ፡ የማመልከቻ ቅፅ (ለንግድ ስራ ሞዴል ፈጠራዎች ብቻ) ……………………………..…….12

መግለጫ ሐ፡ ደንቦችና መመሪያዎች………………………………………………..………15

መግለጫ መ፡ ማመልከቻው በትክክል መሞላቱን ማረጋገጫ ዝርዝር………………………………..17

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ የውሃ፣ የመስኖና የኤሌክትሪክ ሚንስቴር ከኢትዮጵያ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚንስቴር፣ ከተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP)፣ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ ከተባበሩት መንግስታት የልማትየተ.መ.የማ.ል ፈንድን (UNCDF) ጋር በመተባበር በግሎባል ኢንቫይሮንሜንት ፋሲሊቲ (GEF )የገንዘብ ድጋፍ ለቤት ውስጥ ፍጆታና ለማምረቻ አገልግሎት የሚሆን ቀጣይነት ያለው የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ማበረታቻ ፕሮጀክት-ኢትዮጵያ ; የሚል ፕሮጀክት እየተገበረ ይገኛል፡፡ ይህ ፕሮጀክት የኢትዮጵያን የኢነርጂ ስትራቴጂ፣ የኢትዮጵያን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ፣ ኢትዮጵያ ለUNFCCC ያቀረበቻቸውን ብሔራዊ የኮሙኒኬሽን ሪፖርቶች የሚያበለጽግ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በ GEF ድጋፍ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እአአ በ2007 ከተዘጋጀው የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች ዳሰሳ ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ በተጨማሪም "ቀጣይነት ያለው ኢነርጂ ለሁሉም" ከሚለው የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ ማነሳሻዎች ግቦች ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን የሚጠቀሙ እንዲሁም የአፍላሽ/የግሪን ሃውስ/ ጋዝ ልቀታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ተበረታትተውና አድገው አሁን ያለውን ከቅሬተ-አካላት በሚገኝ ነዳጅ እንዲሁም"ቀጣይነትበሌለው ሰብስብ ሕየወት ላይ የተመሰረተውን የኃይል አጠቃቀም እንዲተኩ በማድረግ፤ ከኢነርጂ ጋር በተገናኘ የኢትዮያን የካርቦን ዳይኦክሳይድ ልቀት መጠን በሁለት ሚሊዮን ቶን ያህል በዓመት ለመቀነስ ያለመ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በተለይም የገጠሩ ማህበረሰብ በታዳሽ ኃይሎች ላይ የተመሰረቱ ቴክኖሎጂዎችን ለቤት ውስጥ ፍጆታና ለማምረቻ አገልግሎት አብልጦ እንዲጠቀም የሚያበረታታ ነው፡፡በግምት 200,000 በሚሆኑ አነስተኛ የፀሃይ ፒ ቪ እና 600,000 ያህል የተሻሻሉ የማብሰያ ምድጃዎች ላይ መወዕለ ንዋይ እንዲፈስስ በማስቻል በግምት ስምንት መቶ ሺህ የሚሆኑ አባወራዎች (4 ሚሊዮን ሰዎች) በዚህ ፕሮጀክት አማካይነት ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

ከዚህም አንፃር ለገጠሩ ማህበረሰብ እንዲሁም ለንግድ ድርጅቶች ለማሞቂያ፣ ለመብራትና ለማምረቻ አገልግሎቶች ተስማሚ የሆኑ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን የሚያመርቱና የሚያቀርቡ ድርጅቶች ዕድገት፤ የዚህን ፕሮጀክት አላማዎች ከዳር እንዲደርሱ ለማድረስ ቁልፍ እርምጃ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ፕሮጀክቱ የግሉን ዘርፍ ያሳተፈና ገበያ ተኮር የሆነ አቅጣጫን በመከተል አላማውን ከግብ ለማድረስ ይጥራል፡፡በዚህም መሰረት ፕሮጀክቱ ተወዳድረው ለሚያሸንፉ ኢንተርፕራይዞች የገንዘብ ሽልማት (ለመነሻ የሚሆን)፣ በዓይነታቸው ልዩ የሆኑ ስልጠናዎችንና የቢዝነስ ልማት አገልገሎቶችን በመስጠት የገጠር ኤነርጂ ቴክኖሎጂ እድገትን ለማገዝ አቅዷል፡፡

ይህ የሽልማት ጥቅል የተዘጋጀው የአመራረጥናና የሽልማት አሰጣጥ ሂደቱን ለማመቻቸት ነው፡፡ ጥቅሉ የተዘጋጀው ከታች በክፍል 11 ከተዘረዘሩት የባለድርሻ አካላት/ተቋማት በተወከሉ የባለሙያዎች (በዋና የቴክኒክ) ቡድን ነው፡፡ ዝግጅቱም በተከታታይ ስብሰባዎች የመምረጫ መስፈርቶችን መወሰንን እና ከፕሮጀክቱ አላማዎች ጋር የሚሄዱ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ስብስቦችን መለየትን አካቷል፡፡በተጨማሪም ከአገር ውስጥ ተቋማት ለምሳሌ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚንስቴርንና የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲን እንዲሁም ከተወሰኑ ታዳጊ የአፍሪካ አገሮችና ከህንድ ተሞክሮዎች ተወስደው ተገምግመዋል፡፡ በዚህም መነሻነት ረቂቅ የሽልማት ጥቅል ተዘጋጅቶ ግምገማ እና አስተያየት እንዲሰጥበት ለሁሉም የቡድኑ አባላት እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም ከቡድኑ አባላት የተሰጡ አስተያየቶችንና ማስተካከያዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባትና በማካተት የመጨረሻው የሽልማት ጥቅል ከተዘጋጅ በኋላ ለቡድኑ አባላት ቀርቦ በታህሳስ 08፣ 2009 ዓ.ም. በተደረገ የቡድኑ ስብሰባ ፀድቋል፡፡

## 2. ትርጉም

በዚህ ሰነድ ውስጥ

**የፈጠራ ስራ** ማለት

- በኢትዮጵያ ከገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ጋር የተገናኘ አዲስ ምርት ሂደት(አሰራር) የቢዝነስ ሞዴል መፍጠር ወይም

- በኢትዮጵያ ከገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ጋር የተገናኘ ሆኖ አሁን በሥራ ላይ ባለው ቴክኖሎጂ/አሰራር/የቢዝነስ ሞዴል ላይ ማሻሻያ ወይም ለውጥ ማምጣት ማለት ነው፡፡

**የግሉ ዘርፍ ተቋማት** ማለት

- በመደበኛሽርክና፣ በጥምር፣ ሽርክና፣ በጠቅላላሽርክና፣ በተወሰነሽርክና፣ በሼር ወይም ሃላፊነቱ በተወሰነ የግል ኩባንያ፣ በግለሰብ ባለቤትነት ወይም በአነስተኛና ጥቃቅን በድርጅትነት የተቋቋመ የግል የንግድ ድርጅት ማለት ነው፡፡

**የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ** ማለት

- ከመደበኛ የአሌክትሪክ ስርጭት መስመሮች ውጭ ለሆኑ ወይም ውሱን በሆነ ወይም በተቆራረጠ መልኩ በቀን ከስምንት ሰዓት በታች ኃይል ለሚያገኙ፤ በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ለሚኖሩ ግለሰቦችና ማህበረሰቦች በአነስተኛ ደረጃ ንፁህ የሃይል አቅርቦት ሊሰጡ የሚችሉ፤ከመደበኛ የአሌክትሪክ ስርጭት መስመሮች ጋር ያልተያያዙና በታዳሽ ኃይል ላይ የተመሰረቱ ቴክኖሎጂዎችን/የንግድ ሥራዎችን አዋጭ እንዲሆኑና እንዲሻሻሉ በማድረግ ላይ ያተኮሩ የገጠር ኤነርጂ ቴክኖሎጂዎች ማለት ነው፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ ሽልማት አላማ በአሁኑ ሰዓትበኢትዮጵያ ውስጥ በገጠር ኤነርጂ ቴክኖሎጂ ዙሪያ እየሰሩ የሚገኙ የገጠር ኤነርጂ ቴክሎጂና የቢዘነስ ሞዴሎች የፈጠራ ሥራ ባለቤቶችን ለማገዝና ወደፊትም ተመሳሳይ አዳዲስ ተቋማት እንዲፈጠሩ ለማበረታታት ነው፡፡

## 4. የሽልማት ዘርፎች/ምድቦች

ለአሁኑ የሽልማት ውድድር ሲባል የገጠር ሃይል ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም ሽልማቶች እንደሚከተለው ተከፍለዋል፡-

### 4.1. የፀሃይ የገጠር ኢነርጂቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ፡

ይህ ምድብ ከፀሃይ ፒቪ ሲስተም ጋር የተያያዙ እንደ በፀሃይ ሃይል የሚሰሩ የቤት ውስጥ ሲስተሞች፣ በፀሃይ ሃይል የሚሰሩ የውሃ መሳቢያዎች፣ እና በፀሃይ ሃይል የሚሰሩ ማሞቂያዎችን (በፀሃይ ሃይል የሚሰሩ ምድጃዎችና የውሃ ማሞቂያዎች)ፈጠራ ያጠቃልላል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ምድብ በፀሃይ ሃይል የሚሰሩ ፋኖሶችን/መብራቶችን አያካትትም፡፡

### 4.2. የተሻሻለ የማብሰያ ምድጃ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ፡

ይህ ምድብ የተሻሻሉ የመጋገሪያ ምድጃዎችን፣ በከሰል ወይም በሌሎች ግዝፈ-ህይወት በተገኙ ነዳጆች (biomass) የሚሰሩ ማፍያዎችን፣ በባዮነዳጅ (በኤታኖል/የሚሰሩ ምድጃዎችን፣አየርን አንዲዟዟር በማስገደድ የሚሰሩ ምድጃዎችን ፈጠራ ያካትታል፡፡

### 4.3. የነዳጅ የገጠር ኢነርጂቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ፡

ይህ ምድብ የኢታኖል፣ ከግዝፈ-ህይወት ወይም ከቆሻሻ የሚመረት ከሰል (Briquettes)፣ቀጣይነት ያላቸው የከሰል ማክሰልና የማገዶ እንጨት የፈጠራ ሥራዎችን ያካትታል፡፡

### 4.4. የንፋስ ሃይል የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ፡

ይህ ምድብ ለኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ የሚውሉ አንስተኛ ደረጃ የንፋስ ሞተሮችን እና ለንፁህ ውሃ፣ ለመስኖና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያገለግሉ የንፋስ ወፍጮዎች ፈጠራን የሚያካትት ነው፡፡

### 4.5. የባዮጋዝ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ፡

ይህ ዘርፍ ባዮጋዝ ለቤት ውስጥ ፍጆታ እና ለማምረት ሥራ ካለው አገልግሎት ጋር የተገናኙ የገጠር ኤነርጂ ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡

### 4.6. አነስተኛ የሃይል ስርጭት መረብ(ሚኒ-ግሪድ) የገጠር ኢነርጂቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ፡

ይህ ዘርፍ ለጸሃይ ፒቪ፣ ለአነስተኛ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሃይል፣ እና ለሌሎች ታዳሽ የሃይል ምንጮች የሚያገለግል የሚኒ-ግሪድ የፈጠራሥራዎችን የያዘ ነው፡፡

### 4.7. ለገጠሩ ማህበረሰብ የኢነርጂአጠቃቀም/ውጤታማነት የሽልማት ዘርፍ፡

የሲስተም አጠቃቀም/አመራር፣ ባለው ግብዓትና በሌሎች ነገሮች ተደራራቢና የተሻለ ውጤታማነትን ማምጣት በዚህ ምድብ ውስጥ ይካተታል፡፡

### 4.8. የገጠር ኢነርጂቴክኖሎጂ የንግድ ስራ ሞዴል የሽልማት ዘርፍ፡

ይህ የሽልማት ዘርፍ ከ4.1 - 4.7 ከተዘረዘሩት በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ የገጠር ሃይል ቴክኖሎጂ የንግድ ስራ ሞዴል ፈጠራን ያካትታል፡፡

## 5. በውድድሩ ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችሉ መስፈርቶች

ለዚህ የሽልማት ውድድር በተወዳዳሪነት ተሳታፊ ለመሆን የሚፈልግ የግሉ ዘርፍ ድርጅት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይበቅበታል፡፡

- የፈጠራ ሥራው በክፍል 4 ከተዘረዘሩት ዘርፎች/ምድቦች በአንዱ ምድብ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑት ምድቦች መሆን አለበት፡፡
- የፈጠራ ሥራው ባለቤት ድርጅቱ ወይም የድርጅቱ ባለንብረት መሆን አለበት፡፡
- ፈጠራው የገጠሩ ማህበረሰብን የሃይል ችግር ለመፍታት ለሚደረገው ጥረት ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክት መሆን አለበት፡፡
- ድርጅቱ በፌዴራል እና/ወይም በክልል ባሉ ለንግዱ ዘርፍ በወጡ ህጎች መሰረት የተመዘገበ መሆን አለበት፡፡
- ድርጅቱ ቢያንስ ለአንድ አመት ያህል በገጠር ኤነርጂ ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሰራ መሆን አለበት፡፡
- ድርጅቱ ሁሉንም ተገቢ የመንግስት ግብር የከፈለ መሆን አለበት፡፡
- የድርጅቱ ባለቤትነት (የጥምር ሽርክና ከሆነ ደግሞ የድርጅቱ አብዛኛው የባለቤትነት ድርሻ) የኢትዮጵያዊ/የኢትዮጵውያን መሆን አለበት፡፡

## 6. የሽልማቱ ጥቅል

አሸናፊሆነው የሚመረጡት አመልካቾች/ተወዳዳሪዎችች፡

i. 5,000 የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ የገንዘብ ድጋፍ (መነሻ ካፒታል) ይሸለማሉ፡፡
ii. የተለያዩ ስልጠናዎችና የንግድ ስራ ማሳደጊያ አገልግሎቶች ያገኛሉ
iii. በቀጣይም ዓመታዊ አፈፃፀማቸውንና አቅማቸውን መሰረት በማድረግ፤ በአማካይ እስከ 25,000 የአሜሪካን ዶላር ሆኖ እስከ 40,000 ዶላር ለሚደርስ የገንዘብ ሽልማት ለመወዳደር ሊታጩ ይችላሉ፡፡

## 7. የማመልከት ሂደት

በክፍል 4 ከተዘረዘሩት ምድቦች ውስጥ በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ የቴክኖሎጂ ወይም የንግድ ሞዴል ፈጠራዎች ማመልከት ይቻላል፡፡

ማመልከቻዎች በእንግሊዝኛም ሆነ በአማርኛ መሞላት ይችላሉ፡፡

በክፍል 4 ከተጠቀሱት ውጪ የሆኑ ፈጠራዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

ለአንድ የፈጠራ ሥራ ከአንድ በላይ ማመልከቻ ማቅረብ አይቻልም፡፡

የውድድሩ አላማ የገጠር ሃይል ቴክኖሎጂ ላይ የሚሰሩ ተቋማትን እድገት ማበረታታት ስለሆነ የገንዘብ ሽልማቱ በአንድ የሽልማት መደብ/ዘርፍ ውስጥ በአንድ ድርጅት ብቻ የሚቆም አይደለም፡፡ በአንድ የሽልማት መደብ/ዘርፍ ውስጥ በርካታ አመልካቾች ካሸነፉ እያንዳንዳቸው ሙሉ የሽልማት ጥቅሉን ያገኛሉ፡፡

ለእያንዳንዱ የፈጠራ ስራ በተናጠል ማመልከቻ መቅረብ አለበት፡፡

በአንድ ማመልከቻ ከአንድ በላይ ፈጠራ ማቅረብ አይቻልም፡፡

ማመልከቻዎች የሚሞሉት በመግለጫ ሀ ወይም በመግለጫ ለ በተሰጡት የማመልከቻ ቅፆች መሰረት መሆን አለበት፡፡

አመልካቾች/ተወዳዳሪዎች በመግለጫ ሐ የተገለጹትን ደንቦችና መመሪያዎች ሙሉ በሙሉ መቀበል አለባቸው፡፡

አመልካቾች/ተወዳዳሪዎች የአፈጻጸም ደንቦችና መመሪያዎችን (መግለጫ ሐ) ከፈረሙበት በኋላ ከዋናው ማመልከቻ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡

በማረጋገጫ ዝርዝሩ (መግለጫ መ) ላይ የተዘረዘሩት ሁሉም አስፈላጊ ማስረጃዎች ከማመልከቻ ቅፁ ጋር መቅረብ አለባቸው፡፡

ማመልከቻዎች በተሰጠው የማመልከቻ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡፡

ከተሰጠው የማመልከቻ ጊዜ ውጪ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

## 8. የማመልከቻ ጊዜ

ማመልከቻዎች ከሚያዚያ 23 ቀን 2009 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 23 ቀን 2009 ዓ.ም. ባሉት ሃያ ሦስት የሥራ ቀናት ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 9. ማመልከቻ የሚቀርብበት ቦታ

ማመልከቻዎችን ከሚከተሉት በአንዱ ተቋም ማስገባት ይቻላል፡፡

ሀ. ወረዳ፣ ዞን ወይም ክልላዊ የኢነርጂ ቢሮዎች

ለ. ወረዳ፣ ዞን ወይም ክልላዊ የአካባቢ ቢሮዎች

ሐ. በ ኢ-ሜይል gefret2016@gmail.com

## 10. የአመራረጥ ሂደት

የአመራረጡ ሂደት የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ እና ዋና ማጣሪያ በተሰኙ በሁለት ደረጃዎች ይካሄዳል፡፡

### 10.1. የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ

በዚህ የማጣሪያ ደረጃ ላይ፡-

I. ማመልከቻው ከላይ በቁጥር 5 የተጠቀሱትን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላቱ ይታያል፡፡
II. የማመልከቻው ቅፅ (መግለጫ ሀ እና ለ) በትክክል መሞላቱ ይረጋገጣል፤ እንዲሁም
III. በበማረጋገጫ ዝርዝሩ (መግለጫ ሐ) ላይ የተዘረዘሩት ሁሉም አስፈላጊ ማስረጃዎች ከማመልከቻ ቅጹ ጋር መቅረባቸው ይጣራል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥአንዱ እንኳን ካልተሟላ ማመልከቻው ወዲያውኑ ውድቅ ይደረጋል፡፡

ሆኖም ወደ ዋናው የማጣራት ደረጃ ከመገባቱ በፊት የመጀመሪያው ደረጃ የማጣሪያ ሪፖርት ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴር፤ ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር/ለተ.መ.ል.ፕ በማቅረብ እንዲጸድቅ ይደረጋል፡፡

### 10.2. ዋናው/የመጨረሻው የማጣሪያ ደረጃ

ሁሉም የመጀመሪውን የማጣሪያ ደረጃ ያለፉ ማመልከቻዎች ለዋናው ማጣሪያ ይቀርባሉ፡፡ ዋናው የማጣሪያ ደረጃ የመጨረሻው የአመራረጥ ሂደት ሲሆን በክፍል 13.1 እና 13.2 ላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት በሽልማቱ ዳኞች አማካኝነት ይከናወናል፡፡

## 11. የሽልማት ዳኞች

ሁሉንም የማጣራትና የመረጣ ሂደት የሚያከናውኑት ከሚከተሉት ተቋማት የተወከሉ የሽልማት ዳኞች ናቸው፡፡

i. ከውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴር
ii. ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚንስቴር
iii. ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚንስቴር
iv. ከአካባቢ፣ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚንስቴር
v. ከፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ
vi. ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ-የኤነርጂ ብድር ማስተባበሪያ
vii. ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ
viii. ከአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ
ix. ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ
x. ከሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ
xi. ከመቐለዩኒቨርሲቲ
xii. ከፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ
xiii. ከፌዴራል የከተማ ስራ ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ
xiv. ኢ ዲ ሲ
xv. ከተ.መ.ል.ፕሮግራም

የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴር ወኪል የዳኞች ሰብሳቢ የሚሆን ሲሆን የፕሮጀክቱ ፅ/ቤት ተወካይ ደግሞ ፀሃፊ ይሆናል፡፡

## 12. ውሳኔን ማስጸደቅ

ዋናው የማጣራት ሂደት ሲጠናቀቅ ዳኞች አሸናፊ ብለው የመረጧቸውን ዝርዝር አይተው በጋራ እንዲያጸድቁ ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴር፣ ለተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እና ለኢትዮጵያ የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚንስቴር ያቀርባሉ፡፡

## 13. የመምረጫ መስፈርት

አመልካቾች በማመልከቻ ቅፁ (መግለጫ ሀ ወይም ለ) ላይ ፕሮጀክታቸውን ሲገልፁ በክፍል 13.1 ወይም 13.2 ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚደግፉ አስፈላጊና ተገቢ መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ይመከራሉ፡፡ አመልካቾች የሚያቀርቡትን መረጃ ዋጋ/ጥቅም ይገነዘቡ ዘንድ እያንዳንዱ መስፈርት የሚያስገኘው ከፍተኛ ነጥብ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ተገልጧል፡፡

### 13.1. የመምረጫ መስፈርቶች

ከቁጥር 4.1 እስከ ቁጥር 4.7 ለተዘረዘሩት የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፎች የሚቀርቡ የመወዳደሪያ ማመልከቻዎች በሚከተሉት መስፈርቶች ይመዘናሉ፡፡

| ቁጥር | መስፈርት | ከፍተኛው ነጥብ | አመልካቹ ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ፈጠራ<br>• የፈጠራ ሥራው (ፈጠራው አዲስ ነው ወይስ  የተሻሻለ?)<br>• ለሃገሪቱ ብቸኛ/የተለየ መሆኑ<br>• የቴክኖሎጂው የምክንያታዊነት/ ተጨባጭነት ጥንካሬ (የፈጠራው ቴክኒካዊ የስራ ዝርዝሮች በመሰረታዊ ሳይንስ ላይ የተመሰረቱ ናቸውን?) | 10 | |
| 2 | የፈጠራው ሁኔታ<br>• የምርቱ ዋጋ ተመጣጣኝነት<br>• የሚጠቀመው ግብዓት (resource)መጠን አነስተኛነት<br>• የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች አይነት (ከሃገር ውስጥ ወይስ ከውጭ የተገኙ)<br>• ደህንነትና ለአጠቃቀም ቀላል መሆን<br>• ቶሎ ቶሎ እድሳት የማያስፈልገው ቴክኖሎጂ መሆኑ<br>• በተለያዩ የሃገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች ለማስፋፋት ቀላል መሆኑ<br>• የቴክኖሎጂው ተለኪነት (ለምሳሌ፤ ሜትሪክ ቶን፣ ወዘተ)<br>• ለሀገር በቀል ዕውቀትየሚያበረክተው አስተዋፅዖ<br>• የተፅዕኖው ማረጋገጫ | 20 | |
| 3 | ታሳቢ/ዒላማ ያደረጋቸው ደንበኞች/ተጠቃሚዎች<br>• ትክክለኛ ግለሰቦችን/ማህበረሰቦችን ታሳቢ ማድረጉ (ከቦታና ከብዛት አንፃር)<br>• ቴክኖሎጂውን ለተጠቃሚዎችለማቅረብ የሚጠቀምበት መንገድ ምቹነት<br>• የተፅዕኖው ማረጋገጫ | 15 | |
| 4 | የፈጠራሥራው መባዛትና ቀጣይነት<br>• የማምረት ሂደቱ ቀላል መሆን<br>• በቡድን ውስጥ ስራን የማስፈፀም አቅም<br>• የቴክኖሎጂው ፈጣሪ ከሌሎች ጋር ወይም ብቻውን በመሆን የፈጠራ ሥራው ለመባዛት ያለው ምቹነት፤<br>• ከሚያስፈልጉት ግብዓቶች አንፃር የፈጠራ ስራው ቀጣይነት<br>• የተፅዕኖው ማረጋገጫ | 8 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | ማህበራዊ ተፅዕኖ<br>• ስራ የመፍጠር አቅም<br>• ለሴቶች የሚያመጣው ጥቅም (የስራ ጫናን መቀነስ)<br>• ለአካል ጉዳተኞች የሚያመጣው ጥቅም<br>• የተፅዕኖው ማረጋገጫ | 10 | |
| 6 | ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ<br>• ከውጭ የሚገባ ምርትን የመተካት አቅም<br>• ምርትን ለውጭ ገበያ የማቅረብ አቅም<br>• ድህነትን ለመቀነስ ያለው አስተዋፅዖ<br>• የተፅዕኖው ማረጋገጫ | 10 | |
| 7 | አካባቢያዊ ተፅዕኖ<br>• የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ ያለው አስተዋፅዖ<br>• ለቴክኖሎጂው የሚጠቀመው ቁሳቁስ ቀጣይነት<br>• የኢነርጂ ምንጮች ቀጣይነት<br>• ለኢነርጂ ቁጠባ ያለው አስተዋፅዖ<br>• የተፅዕኖው ማረጋገጫ | 12 | |
| 8 | የንግድ/የቢዝነስእቅድ<br>• የንግድዕቅዱጥንካሬ/አሳማኝነት<br>• የረጅም ጊዜ አዋጭነት - የፈሰሰውን መዋዕለ ንዋይ የመመለስ አቅም | 15 | |

### 13.2. ለገጠር ሃይል ቴክኖሎጂ የንግድ ሞዴል የሽልማት ዘርፍ የመምረጫ መስፈርቶች፡

በክፍል 4.8 ላይ ለተጠቀሰው የገጠር ሃይል ቴክኖሎጂ የንግድ ሞዴል የሽልማት ዘርፍ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በሚከተሉት መስፈርቶች ይመዘናሉ፡፡

| ቁጥር | መስፈርት | ከፍተኛው ነጥብ | አመልካቹ ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | አዲስነት/የመጀመሪያነት፡<br>• ፈጠራው ሌሎች ገበያ ላይ ካሉ ተመሳሳይ ወይም አማራጭ ሞዴሎች ጋር ሲወዳደር ልዩና ተመራጭ የሚያደርገው<br>ፈጠራ፡<br>• ፈጠራው (አዲስ ነው ወይስ የተሻሻለ?)<br>• ለሃገሪቱ ብቸኛ/የተለየ መሆኑ<br>• የቴክኖሎጂው የምክንያታዊነት/ተጨባጭነት ጥንካሬ (የፈጠራው ቴክኒካዊ የስራ ዝርዝሮች በመሰረታዊ ሳይንስ ላይ የተመሰረቱ ናቸውን?)<br>• | 10 | |
| 2 | የፈጠራው ሁኔታ<br>• የሚጠቀመው ግብዓት (resource) መጠን፣ የመሰረተ ልማት አጠቃቀም አነስተኛነት<br>• በፈጠራው ውስጥ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ያለው ሚና (ፈጠራው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ይዘት አለው?)<br>• የሃገሪቱን ገጠራማ ቦታዎች የማዳረስ አቅም<br>• የንግድ ሞዴሉ የሚሰራባቸው የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች | 20 | |
| 3 | ታሳቢ/ዒላማ ያደረጋቸው ደንበኞች/ተጠቃሚዎች<br>• ትክክለኛ ግለሰቦችን/ማህበረሰቦችን ታሳቢ ማድረጉ (ከቦታና ከብዛት አንፃር)<br>• ለገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሞዴሉ ትክክለኝነት/ተገቢነት | 15 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | የፈጠራ ሥራው መባዛትና ቀጣይነት<br>• በቡድን ውስጥ ስራን የማስፈፀም አቅም<br>• ከሌሎች አካላት ጋር በሽርክና ለመስራት ያለው ዕድል<br>• የንግድ ሞዴሉ ቀጣይነት (ከሚያስፈልጉት ግብዓቶች አንፃር)<br>• ፈጠራው በሌሎች ተመሳሳይ ገበያዎች ላይ በቀላሉ ተግባራዊ ሊደረግ የሚቻልበት ዕድል | 8 | |
| 5 | ማህበራዊ ተፅዕኖ<br>• ስራ የመፍጠር አቅም<br>• ለሴቶች የሚሰጠው ጥቅም (የስራ ጫናን መቀነስ)<br>• ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ጥቅም<br>• ፈጠራው ዒላማ በተደረገው ማህበረሰብና ከዚያም በሰፋ ሁኔታ አዎንታዊ ወይም ተፈላጊ ለውጦችን ለማምጣት ያለው አቅም | 10 | |
| 6 | ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ<br>• ፈጠራው በገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮችን በበቂ ሁኔታ ለመፍታት የመቻሉ መጠን<br>• ድህነትን ለመቀነስ ያለው አስተዋፅዖ<br>• በንግድ ስራው ውስጥ የገጠሩን ማህበረሰብ ማሳተፍ<br>• የተፅዕኖው ማረጋገጫ | 10 | |
| 7 | አካባቢያዊ ተፅዕኖ<br>• የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ ያለው አስተዋፅዖ<br>• ቁሶችን፣ ሃይልንና የሃይል ምንጮችን ቀጣይነትን በሚያረጋግጥ መልኩ በመጠቀም ረገድ ያለው አስተዋፅዖ<br>• የተፅዕኖው ማረጋገጫ | 10 | |
| 8 | የንግድ/የቢዝነስእቅድ<br>• የንግድ ዕቅዱ ጥንካሬ/አሳማኝነት<br>• የረጅም ጊዜ አዋጭነት - የፈሰሰውን መዋዕለ ንዋይ የመመለስ አቅም | 17 | |

**<u>ጠቃሚ መረጃ</u>**

ለሽልማት በቀረቡት ማመልከቻዎች ላይ በዳኞች የሚተላለፉ ውሳኔዎች የመጨረሻ ስለሆኑ ማንኛውም ተጨማሪ ጥያቄ/ግንኙነት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**<u>ተጨማሪ መረጃ</u>**

ለተጨማሪ መረጃ ጥያቄዎን ለ ውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር ዳይሬክቶሬት በስልክ ቁጥር 251-116-63-83-90 ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**መግለጫ ሀ፡ የማመልከቻ ቅፅ (ለገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ብቻ)**

| **1.** | **የሽልማት ዘርፎች**<br>(እባክዎን በሚወዳደሩበት የሽልማት ዘርፍ ፊት ለፊት የ "x" ምልክትን ያስቀምጡ) | የተመረጠው ዘርፍ |
|---|---|---|
| 1.1 | የፀሃይ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ | |
| 1.2 | የተሻሻለ የማብሰያ ምድጃ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ | |
| 1.3 | የነዳጅ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ | |
| 1.4 | የንፋስ ሃይል የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ | |
| 1.5 | የባዮጋዝ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ | |
| 1.6 | አነስተኛ የሃይል **ስርጭት መረብ** (ሚኒ-ግሪድ) የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ዘርፍ | |
| 1.7 | ለገጠሩ ማህበረሰብ የኢነርጂ/የሃይል አጠቃቀም ውጤታማነት የሽልማት ዘርፍ | |

| **2.** | **የንግድ ተቋሙ አጠቃላይ መረጃ** | |
|---|---|---|
| 2.1 | የተቋሙ ስም | |
| 2.2 | የታደሰ የንግድ ምዝገባ ቁጥር | |
| 2.3 | የስልክ ቁጥር | |
| 2.4 | የኢ-ሜይል አድራሻ | |
| 2.5 | ክልል | |
| 2.6 | ከተማ/የገጠርዞን | |
| 2.7 | ወረዳ | |
| 2.8 | ቀበሌ | |
| 2.9 | የቤት ቁጥር | |

| 3. | የተቋሙ ባለቤት/ሃላፊ አጠቃላይ መረጃ | |
|---|---|---|
| 3.1 | የባለቤቱ/የሃላፊው ስም | |
| 3.2 | ፆታ | |
| 3.3 | ዕድሜ | |
| 3.4 | የትምህርት መስክ | |
| 3.5 | የትምህርት ደረጃ | (ለምሳሌ፡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ት፣ ቴክኒክና ሙያ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ወዘተ ) |
| 3.6 | ስልክ ቁጥር | |
| 3.7 | ኢ-ሜይል አድራሻ | |
| 3.8 | ክልል | |
| 3.9 | ከተማ/የገጠር ዞን | |
| 3.10 | ወረዳ | |
| 3.11 | ቀበሌ | |
| 3.12 | የቤት ቁጥር | |

| 4. | የፈጠራሥራው መግለጫ (ቢበዛ ሶስት ገፅ) |
|---|---|
| | የፈጠራው መግለጫ፡የሚከተሉትን የሚያሟላ መሆን አለበት<br>• የፈጠራውን ቁልፍና ጎልተው የሚታዩ ባህሪዎቹን /ይዘቶቹን የሚያሳይ<br>• ፈጠራው የሚያመጣቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽእኖዎች የሚያብራራ<br>• በገበያ ውስጥ ካሉ ተወዳዳሪዎች እንዴት እንደሚለይ የሚያሳይ<br>• የሚያመጣው ተጽእኖ ይሰፋ ዘንድ ፈጠራው ሊተልቅና ሊባዛ የሚችል መሆኑን የሚያሳይ<br>• ለረጂም ጊዜ ቀጣይነት ያለው ፕሮጀክት መሆኑን የሚያሳይ<br>• ለውድድር ያቀረቡት የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ወይም የንግድ ሞዴል በሥራ ላይ ያሉትን መፍትሔዎች እንዳሉ የሚደግም ሳይሆን ልዩ የሚያደርገው እሴት እንዳለው በግልፅ የሚያሳይ<br>• ድርጅትዎ ሲቋቋም የነበሩትንና አሁንያሉትን የሰራተኞች ብዛትየሚያመለክት<br><br>**ባጠቃላይ ማመልከቻዎ ለሽልማት የተቀመጡትን መስፈርቶች ምን ያህል እንደሚያሟላ በግልፅ ለማሳየት ይሞክሩ፡፡** |

| 5. | የንግድ ዕቅድ (ቢበዛ አንድ ገፅ) |
|---|---|
| | የንግድ ዕቅድዎ የሚከተሉትን ማሳየት አለበት፡<br>• ምን ያህል መነሻ ገንዘብ እንደሚያስፈልገውና ገንዘቡም እንዴት እንደተገኘ (ሊገኝ እንደታሰበ)<br>• በቅድሚያ መሟላት ያለባቸውን ለመግዛት ምን የፋይናንስ ምንጭ ለመጠቀም እንደታሰበ<br>• የፈሰሰው መዋዕለ ንዋይ የሚመለስበት ጊዜ<br>• ተግዳሮቶች ካሉ - እና እንዴት ስለመፍታት እንደታሰበ<br>• ስትራቴጂዊ አቅጣጫዎች (ምርት፣ ሽያጭ፣ ማስፋፊያ፣ ወዘተ) |

| | |
|---|---|
| | • የማቀድ አቅምዎን የሚያሳይ ሌላ ማንኛውም ዓይነት መረጃ፣ወዘተ |
| **6.** | **የሽልማት ገንዘብ አጠቃቀም ዕቅድ** |
| | እባክዎን ሽልማቱን ቢያሸንፉ ገንዘቡን እንዴት ሊጠቀሙ እንዳሰቡ በደንብ ይግለፁ፡፡ |
| **7.** | **የተጽዕኖማረጋገጫ (ቢበዛግማሽገጽ)** |
| | ከሚከተሉት በአንድ ወይም በብዙ መንገድ ተጽዕኖውን ማረጋገጥ ይቻላል<br>• የተቆጠበ/የዳነ የጊዜ፣ የጉልበት፣ የነዳጅ ወይም የቁሳቁስ መጠን<br>• የተቀነሰ የቆሻሻ መጠን<br>• የተጨመረ/ያደገ ውጤታማነት<br>• ትርፋማነት፣ የንብረት መጠን፣ እና የድርጅቱ ሰራተኞች ብዛት … ወዘተ |

**መግለጫ ለ፡ የማመልከቻ ቅፅ (ለንግድ ስራ ሞዴል ፈጠራዎች ብቻ)**

| **1.** | **የሽልማት ዘርፎች**<br>(እባክዎን የሚወዳደሩበት የሽልማት ዘርፍ ፊት ለፊት የ “x” ምልክት ያስቀምጡ) | የተመረጠው ዘርፍ |
|---|---|---|
| 1.1 | የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የንግድ ሞዴል የሽልማት ዘርፍ | |

| **2.** | **የንግድ ተቋሙ አጠቃላይ መረጃ** | |
|---|---|---|
| 2.1 | የተቋሙ ስም | |
| 2.2 | የታደሰ የንግድ ምዝገባ ቁጥር | |
| 2.3 | የስልክ ቁጥር | |
| 2.4 | የኢ-ሜይል አድራሻ | |
| 2.5 | ክልል | |
| 2.6 | ከተማ/የገጠር ዞን | |
| 2.7 | ወረዳ | |
| 2.8 | ቀበሌ | |
| 2.9 | የቤት ቁጥር | |

| **3.** | **የተቋሙ ባለቤት/ሃላፊ አጠቃላይ መረጃ** | |
|---|---|---|
| 3.1 | የባለቤቱ/የሃላፊው ስም | |
| 3.2 | ፆታ | |
| 3.3 | ዕድሜ | |
| 3.4 | የትምህርት መስክ | |
| 3.5 | የትምህርት ደረጃ | (ለምሳሌ፡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ት፣ ቴክኒክና ሙያ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ወዘተ ) |
| 3.6 | ስልክ ቁጥር | |
| 3.7 | ኢ-ሜይል አድራሻ | |
| 3.8 | ክልል | |
| 3.9 | ከተማ/የገጠር ዞን | |

| | | |
|---|---|---|
| 3.10 | ወረዳ | |
| 3.11 | ቀበሌ | |
| 3.12 | የቤት ቁጥር | |

## 4. የፈጠራው መግለጫ (ቢበዛ ሶስት ገፅ)

የፈጠራው መግለጫ፡ የሚከተሉትን የሚያሟላ መሆን አለበት

- የፈጠራውን ቁልፍና ጎልተው የሚታዩ ባህሪዎቹን /ይዘቶቹን የሚያሳይ
- የንግድ ስራ ሞዴሉን ዓይነት
- ፈጠራው የሚያመጣቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽእኖዎች የሚያብራራ
- ከሌሎች የቢዝነስ ሞዴሎች እንዴት እንደሚለይ የሚያሳይ
- ለረጅም ጊዜ ቀጣይነት ያለው ፕሮጀክት መሆኑን የሚያመለክት
- የትኛውን የገበያ ፍላጎት እንደሚያሟላና በገበያው ውስጥም በምን ምክንያት አስፈላጊ እንደሆነ የሚያሳይ
- ድርጅትዎ ሲቋቋም የነበሩትንና አሁንያሉትን የሰራተኞች ብዛትየሚያመለክት

**ባጠቃላይ ማመልከቻዎ ለሽልማት የተቀመጡትን መስፈርቶች ምን ያህል እንደሚያሟላ በግልፅ ለማሳየት ይሞክሩ፡፡**

መግለጫው፡

- የንግድ ስራ ሞዴሉን ቁልፍ ልዩ ባህሪያት/ይዘቶች አሳይ
- የንግድ ስራ ሞዴሉ ዓይነት
- የንግድ ስራው የሚያመጣቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ለውጦች አብራራ
- ከሌሎች የንግድ ስራ ሞዴሎች ልዩ የሚያደርጉትን ነጥቦች ግለፅ
- ለረጂም ጊዜ የማያቋርጥ ፕሮጀክት መሆኑን አሳይ
- ስትጅምር የነበሩህን የሰራተኞች ብዛትና አሁን ያሉህን ግለፅ

ባጠቃላይ ማመልከቻህ ለሽልማት የተቀመጡትን መስፈርቶች ምን ያህል እንደሚያሟላ በግልፅ አሳይ፡፡

## 5. የንግድ ዕቅድ (ቢበዛ አንድ ገፅ)

ዕቅድዎ የሚከተሉትን ማሳየት አለበት፡

- ዋና/ወሳኝ አቅሞችን
- ተቋማዊ አደረጃጀት
- የገንዘብ ዝግጅቶች
- የወጪ ማሳያ
- የገቢ ሞዴል
- ምን ያህል መነሻ ገንዘብ እንደሚያስፈልገውና እንዴት እንደተገኘ (ሊገኝ እንደታሰበ)
- በቅድሚያ መሟላት ያለባቸውን ለመግዛት ምን የፋይናንስ ምንጭ ለመጠቀም እንደታሰበ
- ሊከሰቱ የሚችሉ ተግዳሮቶች ካሉና እንዴትስ መፍታት እንደታሰበ
- ታሳቢ የተደረጉ ደንበኞች፣ከደንበኞች ጋር የሚኖር ግንኙነት
- የንግድ (የማከፋፈያመስመሮችና) የሽሪኮች (ካሉ)መረቦች
- ስትራቴጃዊ አቅጣጫዎች (ምርት፣ ሽያጭ፣ ማስፋፊያ፣ ወዘተ)

የማቀድ አቅምዎን የሚያሳይ ሌላ ማንኛውም ዓይነት መረጃ፣ወዘተ

## 6. የሽልማት ገንዘብ አጠቃቀም ዕቅድ

እባክዎን ሽልማቱን ቢወስዱ ገንዘቡን እንዴት ሊጠቀሙ እንዳሰቡ በደንብ ይግለፁ፡፡

| 7. | **የተፅዕኖ ማሳያ (ቢበዛ ግማሽ ገፅ)** |
|---|---|
| | ከሚከተሉት በአንድ ወይም በብዙ መንገድ ውጤቱን ማሳየት ይቻላል<br>• የተቆጠበ/ኩብክነት የዳነ የጊዜና የጉልበት መጠን<br>• የተቀነሰ የቆሻሻ መጠን<br>• የተጨመረ/ያደገ ውጤታማነት<br>• ትርፋማነት፣ የንብረት መጠን፣ እና የድርጅቱ ሰራተኞች ብዛት … ወዘተ<br>• የተሳኩ አላማዎች/ግቦች<br>• የደንበኞች እርካታ |

## መግለጫ ሐ፡ ደንቦችና መመሪያዎች

1. አመልካቾች ማመልከቻቸውን ለውድድሩ ሲያስገቡ በማመልከቻቸው ውስጥ ስለተካተቱት መረጃዎች እውነተኛነትና ትክክለኛነት ሃላፊነትና ዋስትና ይወስዳሉ፡፡ አመልካቾች ያካተቷቸው ማብራሪያዎችና መረጃዎች አውነት ያልሆኑ፣ ልክ ያልሆኑና የተሳሳተ መረጃ የሚያስተላልፉ ሆነው ከተገኙ የሽልማት ዳኞች ባላቸው ሙሉ የመወሰን መብት መሰረት በማንኛውም የውድድሩ ደረጃ ወቅት አመልካቹን/ አመልካቿን/ አመልካቾቹን ከውድድር ሊያሰናብቱ ይችላሉ፡፡
2. አመልካቾች በማመልከቻቸው ውስጥ የራሳቸውን የፈጠራ ስራ ብቻ በኢጋዥነት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
3. ሁሉም አመልካቾች በማመልከቻቸው ውስጥ ያሉ ሃሳቦችና ቁሳቁሶች የግልና የአይምሮ ንብረት መብትን ጨምሮ የማንኛውም የሶስተኛ ወገን መብትን እንዲሁም የቅጅ መብትን፣ የንግድ ምልክትን፣ የፈጠራ መብትን ወይም በሌሎች በህግ የተጠበቁ መብቶችን የማይጥሱ መሆን አለባቸው፡፡ ነገር ግን በማመልከቻው ውስጥ የሶስተኛ ወገን የቅጅ መብት፣ የንግድ ምልክት ወይም ሌሎች የአይምሮ መብቶችን የያዙ ቁሳቁሶች የተካተቱ ከሆነ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ህጋዊ ፈቃድ፣ የባለመብቱ ፈቃደኝነትና ነፃ መሆኑን ማረጋገጫዎች ስለመሆናቸው አመልካቾች ሃላፊነትና ዋስትና ፡፡
4. የሽልማት ዳኞች ማንኛውንም በአመልካቾች ይፋ የተደረገን፣ ማብራሪያ የተሰጠበትን ወይም ውይይት የተደረገበትን መረጃ በፎቶኮፒ፣ በፎቶ፣ በምስልና በድምፅ ቀርፀው ሊይዙ አስከቻሉ ድረስ አመልካቾች ለውድድር ባቀረቧቸው ፈጠራዎች የአይምሮ ንብረት ባለመብትነታቸውን የተጠበቀ ነው፡፡
5. የኢትዮጵያ የውሃ የመስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴር እና የተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራም ስለተመረጡት ተወዳዳሪዎች ለህዝብ አንዳንድ መረጃዎችን እንዲሁም ፎቶ፣ የህይወት ታሪክ፣ የንግድ ዘርፍ፣ የድርጅት ዓርማ፣ የስራ ስኬት ባጭሩ የመሳሰሉትንና ስለተወዳደሩበት የፈጠራ ስራ ህዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች በተለይም በድረ-ገፆቻቸው፣ በመፅሄቶቻቸው፣ በአጫጭር የፅሁፍ መግለጫዎቻቸው፣ በመደበኛ ሪፖርቶቻቸው ወዘተ የማውጣት መብት አላቸው፡፡
6. ማመልከቻ ከማስገባትና በሚጠየቁበት ጊዜ ብቻ ተጨማሪ መረጃ ከማቅረብ ውጭ፤ አመልካቾች ወይም በአመልካቾች ስም ሌላ ሰው የውድድሩን ውጤት ለማስቀየር በማሰብ ማንኛውንም የሽልማት ዳኞች አባል እንዲሁም የውሃ የመስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴር እና የተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራም ተወካዮችን ማግኘት ወይም ለማግኘት መሞከር ከውድድር ያስርዛል፡፡
7. አመልካቾች ማንኛውንም አይነት ሀ) ማጭበርበር፣ አደራ መብላት ወይም ስርቆት ለ) መጥፎ ባህሪይ እና ሐ) ሆን ተብሎ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ሽልማቱን አላማዎች በሚቃረን መልኩ ማንኛውም አይነት የህግና የደንብ ጥሰት ከፈፀሙ ወይም ስለመፈጸማቸው የሚያመላክት ነገር ከተገኘ ወዲያወኑ ከውድድሩ እንዲሰረዙ ይደረጋል፡፡
8. የውሃ የመስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴር እና የተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራም በተወዳዳሪዎችና በሶስተኛ ወገን መካከል ለሚደረጉ ግንኙነቶች/ድርድሮች/ዝግጅቶች ሃላፊነት አይወስዱም፡፡
9. በሁሉም ዘርፍ የሚወዳደሩ አመልካቾች የውሃ የመስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴር እና የተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራም ባላቸው ብቸኛና ፍፁም መብት በየጊዜው ሊያሻሽሉት በሚችሉት የገጠር ኤነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ህግ መስማማት ይገባዋቸል፡፡
10. አንድ አመልካች ማመልከቻውን በሚያስገባበት ጊዜ ሀ)ለገጠር ኤነርጂ ቴክኖሎጂ የሽልማት ውድድር ማመልከቻ ከማስገባት ጋር በተያያዘ ለ) ማንኛውንም ዓይነት ሽልማት ከማግኘት ወይም በውድድሩ ውስጥ ተሳታፊ ከመሆን ወይም ከውድድሩ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ምክንያት (ወደ ውደድሩ/ሽልማቱ ቦታ መጓጓዝን ጨምሮ) ወይም ሐ) የአመልካቹን ምስል ወይም በማመልከቻው ውስጥ የተካተቱን ወይም ከውድድሩ ጋር የተያያዙትን በመገኛኛ ብዙሃን አማካይነት ወይም በሌላ መልኩ በሚደረግ ስርጭት፣ ምክንያት የግለሰብ መብትን በመጣስ፣ ስም በማጉደፍ፣ በንግድ ምልክት፣በቅጅ መብት፣በአዕምሮ ንብረት ባለቤትነት መብት፣ እንዲሁም የፈጠራ መብትን ወይም በሌሎች በህግ የተጠበቁ መብቶችን በመጣስ ምክንያት፣በጥቅም ዲዛይን መብቶች፣ በንብረት መጥፋት፣ ወይም በሰው ላይ በሙሉም ሆነ በከፊል፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚደርሱ ጉዳቶች የተነሳ ለሚመጡ ማንኛውም ዓይነት ተጠያቂነቶች፣ ኪሣራዎች፣ ጥፋቶች፣ ኃላፊነቶች፣ ወዘተ ሙሉ ኃላፊነቱን አመልካቹ/አመልካቿ/ አምልካቾቹ ይወስዳል/ትወስዳለች/ይወስዳሉ፡፡ በመሆኑም አመልካቹ የውሃ የመስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴርን እና የተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራምን እንዲሁም የነዚህን መሥሪያ ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች፣ ዳይሬክተሮች፣ ሰራተኞች፣ ተወካዮች፣ አማካሪዎችና በሽልማት ዳኝነት ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦችን ከማንኛውም ዓይነት ተጠያቂነት ነፃ አድርጓል፡፡
11. አመልካቾች በማመልከቻቸው ውስጥ በሰበሰቡትና ባከማቹተ መረጃ ውስጥ ባለ ስህተት ወይም ከማመልከቻው ሂደት፣ ከውድድሩ ወይም ከሽልማቱ ጋር በተገናኘ በህትመት፣ በስርጭት ወይም በማስታወቂያ ጊዜ በተፈጠረ ስህተት/ግድፈት ምክንያት ማንኛውም ዓይነት ጉዳቶች፣ ጥፋቶች፣ ወይም ኪሣራዎች በአመልካቾቹ ላይ ቢደርሱ ወይም ደርሰውብናል በሚል ወይም ሊደርሱብን ይችላሉ ከሚሉ ተጠያቂነቶች አመልካቾች የውሃ የመስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴርን እና የተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራምን ሙሉ ለሙሉ ከተጠያቂነት ነፃ አድርገዋል፡፡

12. እያንዳንዱ ተወዳዳሪ የመወዳደሪያ ቁሳ ቁሶችን (materials) ለሽልማት ዳኞች ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡ የውሃ የመስኖና ኤሌክትሪክ ሚንስቴር እና የተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራም በአመልካቾች ለቀረቡና ውይይት ለተደረገባቸው ፋይሎችና መረጃዎች ምንም አይነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በምስጢር የመጠበቅ ዋስትና አይሰጡም፡፡ የውድድር ዳኞችም ከውድድር ቁሳቁሶች (materials) ጋር በተያያዘ የምስጢር መጠበቅ ስምምነት አይፈርሙም፡፡
13. የሽልማት አወሳሰዱ እዚህ በተመለከቱት የውድድር ህጎች፣ ሰነዶች እና ስምምነቶች ውስጥ የተዘረዘሩትን ሁሉንም መስፈርቶች የሽልማት ተቀባዩ በማሟላቱ ላይ የተወሰነ/የተመረኮዘ ነው፡፡

እኔ ________________________________________________________________________ ከላይ የተዘረዘሩትን ደንቦችና መመሪያዎች አንብቤ እና ተረድቼ በደንቦችና መመሪያዎች ለመመራት በእኔ እና/ወይም በወከልኳቸው ሰዎች ስም መስማማቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ፊርማ፡ ____________________________________________________________

ቀን፡ ____________________________________________________________

## መግለጫ መ፡ ማመልከቻው በትክክል መሞላቱን ማረጋገጫ ቅፅ

ምንም ነገር አለመርሳትዎን እርግጠኛ ለመሆን እባክዎትን ያረጋግጡና የሚከተለውን ሰንጠረዥ ይሙሉ፡፡

| **ቁጥር** | **አጠቃላይ መመዘኛ** | **አዎ** | **የለም** |
|---|---|---|---|
| **1** | የማመልከቻ ቅፁን በትክክል ሞልተዋል **?**<br><br>(መግለጫ ሀ ወይም ለ) | | |
| **2** | ደንብና መተዳደሪያውን ፈርመው አያይዘዋል **?**<br><br>(መግለጫ ሐ) | | |
| **3** | ስልጣን ካለው የመንግስት አካል የተሰጠ የታደሰ የንግድ ፈቃድ አያይዘዋል **?** | | |
| **4** | ድርጅትዎ ላለፈው አንድ ዓመት ያለበትን የገንዘብ አቋም የሚያሳይ ማንኛውንም<br><br>አይነት ማስረጃ አያይዘዋል **?** | | |
| **5** | ለፈጠራ ስራዎ የባለቤትነት መብት ማስረጃ ኮፒ አያይዘዋል **?** | | |
| **6** | የሌሎች አጋዥ ሰነዶች ኮፒዎችን አያይዘዋል **?** | | |